የካቲት 12ቀን 2009ዓ.ም(19.02.2017)

# <u>ዓላማውን የሳተና ግራ የተጋባ አካሄድ ጥቅሙ ለአማራው ሳይሆን ለጠላት ነው!</u>

ዛሬ በመጠኑ መዳሰስ የፈለግኩት በስብሰባዎች፣በፌስቡክ፣በፓልቶክ በድረገፅ ወዘተ፣ የሚወረወሩትን አፍራሽ አነጋገሮችና ውጣ ውረዶች ይሆናል።

-በአንድ ስብሰባ ላይ ከተነገሩት መካከል አንዳንዶቹን እንጥቀስ፣ አንድ የምናደንቀው ወንድማችን እንዲህ ይላል " ሁላችንም መሪ አንሁን፣መሪና ተመሪ መሆን እንቻል "ሲል ተደምጧል።ይህ ግሩምና የሚደነቅ አመለካከት ከመሆኑም በተጨማሪ ቅንነትንም አንፀባርቋልና ልናከብረው ይገባል።

-በተቃራኒው ሌላው ስብሰባውን የመራው ደግሞ ከዕለቱ ተሰብሳቢዎችም ሆነ ከመድረኩ ተጋባዦች ንግግሮች ጋር ያልተዛመዱ አካሄዶችን እንዲህ ሲል አሥደመጠ፣ " እናንተ የምታውቁት የ60ውን ሊሆን ይችላል፣የእኛንም አክብሩልን እንዳላዋቂ አትቁጠሩን"፣ካለ በኋላ አንዳንድ ሰዎች በመካከል ከተናገሩ በኋላ ይኸው ግለሰብ ማጠናከሪያ ሲሰጥ " የ40ና የ50ን ላለመድገም" አለ። ለነገሩ አሁንም በተዘዋዋሪ እየተደገመ ነው።ይህ ግለሰብ ይህን የሚለው ከወጣት እሥከአንጋፋ ያሉትን የድርጅት ሰዎች በአንድ በኩል ወደአንድነት እንዲመጡ ግፊት በማድረግ ገንቢ ሥራ በመሥራት ሲሆን በሌላ በኩል "እናንተ የምታውቁት የ60ውን" የሚል ትህትና የጎደለው አፍራሽ ንግግር በመጠቀም ነበር።ገንብቶ ማፍረስ ተገቢ አይሆንም፣ጥንቃቄ ያሻል።ይህ አካሄድ ከጥንቱ ፊውዳል፣ላብ አደር፣ከበርቴ ትምክህተኛ፣ወዛደር ወዘተ ከሚለው አነጋገር በምንም አይለይም።

ይህ ወጣት ነኝ ባይ ምንም እንኳን ታሪኩን በጥልቀት ባያውቀውም፣ሥለ60ዎቹ አጥፊነት አፉን ሞልቶ በተናገረበት የስብሰባ ቦታ ላይ የ60ዎቹንና ወጣቶቹን ሽምግሎ አንድ ለማድረግ በተጠራው ሥብሰባ ላይ ነበር። እየተሳደበ መሽምገል፣ምን ዓይነት ሽምግልና ይሆን ብዬ ሥከታተል እንደጠረጠርኩት ፍሬ ሳያፈራ ቀረ።

አንድን ነገር ሥንናገር በአየር የሚበሩ ንግግሮችን እየጠለፍን ሳይሆን "ማን ይናገር የነበረ፣ ማን ያርዳ የቀበረ" የሚል ብሂላችንን ህያው በማድረግ አለያም ጉዳዩን በጥልቀት ከተረዳን በኋላ ጥንቃቄን በተላበሰ መልኩ ቢሆን ይመረጣል።

ይህ ወጣት ነኝ ከሚል የስብሰባው መሪ የተሰነዘረው ቁልጭ ያለ አነጋገር የሚያሳዩኝ በወጣቱና በአንጋፋው መካከል ትልቅ ክፍተት እንዲፈጠር፣ወይም እንደተፈጠረ ወይም እንዳለ ነው።

**እስኪ በቅድሚያ የ60ዎቹ ከሚወቀሱባቸው ቁምነገሮች አንዱን ብቻ አሥጨብጠን እንለፍ።**

"በኢትዮጵያ አቆጣጠር በ1957ዓም ከባድ ርሀብ በአገሪቱ ገብቶ በብዙ ሽህ የሚቆጠር የሰው ህይወት አጥፍቷል።ይህም ረሀብ እንዳችም ቦታ እንዳይደርስ በባለሥልጣናት ተከላካይነት ሆን ተብሎ ታፍኖ ቀርቷል። በዓይናችንም እሬሳ በሬሳ ላይ ተደራርቦ፣የሬሳ ክምር በቅርበት አይተናል።

| |
|---|
| አንዱ እየበላ ሌላው በርሀብ አለንጋ ተገርፎ ሲሞት፣ይህንን ዓይነት አረመኔነት ማዬት ያስቆጣል። ከፊሎቻችን ሐምሌና ነሐሴ በመጣ ቁጥር በየቤታችን የሚበላ እየጠፋ በየዓመቱ በረሀብ አለንጋ እየተገረፍን፣ከረሀብ አፋፍ ላይ በመቆም በሰቀቀን ያደግንና ከሞት የተረፍን በመሆናችን መጮህንና ትግልን መርጠናል።<br>ለወገን አቅም እስከቻለ መጮህም እንደተጠበቀ ሆኖ፣ ትምህርት ቤት የገባንም ከዚህ አሰቃቂ ረሀብ ለማምለጥ ከትምህርቱ ጋር የሞት የሽረት ግብ ግብ ገጥመን በተሻለ ውጤት ማለፍ የግድ ነበር። እዚያ እስከሚደረስ ድረስ የነበረው ውጣ ውረድ አይነሳ።ይህ ነበር ረሀቡን የቀመስነው ሰዎች አኗኗር።ከእኛ አኗኗር በባሰ ደረጃ የነበሩት ወገኖቻችን ደግሞ አልቀዋል።በዚህ አሰቃቂ ጎዳና ያላለፈ ቢነገረውም ለእሱ ወይም ለእሷ ተረት ተረት ሊመስል ይችል ይሆናል። |

አሁንም ረሀቡ እየባሰ፣እየጠናበትና እየሰፋ እስከ 1965ዓም ሄደ።26 እንደራሲዎች ተሰባስበው ለሕዝቡ የግብር ምህረት እንኳን እንዲደረግለት ቢጠይቁ፣ የነበረው መንግሥት እንደለመደው ጆሮ ዳባ ልብስ አለው።አቤቱታው እስከ ጠቅላይ ሚኒስቴር ቢሮ ደረሰ። ከጠቅላይ ሚኒስተሩ ወደሚመለከታቸው ቢተላለፍም፣በየደረሰበት በነበረው ቢሮክራሲ ቢንከራተትም ተውጦ ቀረ እንጅ ምንም መፍትሔ አልተገኘለትም። ይህ ሁሉ ሲሆን ሕዝብ እንደቅጠል ይረግፋል።

በውጭ አገር የነበረው ኢትዮጵያዊ ህብረተሰብ አቤቱታውን ያጦፋል።በምንኖርበት አውሮፓ ሠላማዊ ሰልፍ በሚደረግበት ወቅት ረሀቡን ያጋለጠው የጆናታን ዲምብልቢ የሴት ጓደኛው እንዳጋጣሚ በአካባቢ ሥለነበረች ቀርባ የምን ሰልፍ እንደሆነ ትጠይቃለች፣ረሀቡ ከተከሰተበት አካባቢ ከመጡት ተማሪዎች መካከል ዝርዝር ግንዛቤ አገኘች። የዕረፍት ጊዜዋን ጨርሳ ወደለንደን ሥትመለስ ለጓደኛዋ ለዲምቢልቢ "በ1965ዓም በምዕራብ አፍሪካ በርሀቡ ላይ ሠርተሀል፣ተመሳሳይ ሁኔታ ኢትዮጵያ እንደተፈጠረ ሠምቼ መጣሁ" ትለዋለች።እሱም ይህንን ዜና እንደሰማ ሳያመነታ ተነሥቶ ወደ ኢትዮጵያ ሄደ።

በግዴለሽነትና በበሰበሰ ቢሮክራሲ ተሸብቦ አመታትን ያሥቆጠረውን የረሀብ ሠቆቃ የራሳችን ጉዶች ደብቀው ቢያቆዩትምና ባያወጡትም ነጭ ከለንደን ሄዶ አወጣው። ከሁሉም የበለጠ ሆድ የሚያደማው ደግሞ ረሀብ መኖሩን ገሀድ አድርጎ የተወሰነ ነፍስ ከማዳን ይልቅ፣

በኢትዮጵያ መንግሥት ባለሥልጣናት አማካይነት ፊልሙን ለመቀማት የተለያዩ ሙከራ በዲምቢልቢ ላይ መደረጉ ነው።
በተለይም **የማስታዎቂያ ሚኒስቴር የነበረው ዶክተር ተስፋዬ ገብረ እግዚአብሔር** "በመንግሥት ያልተፈቀደ ነው"በማለት አሥፈራርቶ ለመንጠቅ ሙከራ አድርጎ ነበር።ይኸው ሚኒስቴር "የኢትዮጵያን ቆሻሻ ለዓለም ሕዝብ ለማሳዬት ትፈልጋለህ?" በማለት ዲምብልቢን ቢከራከረውም "እኛ ያነሳነውን ፊልም በቴክኒክ ችግር ምክንያት እዚህ አጥበን ለማሳዬት አንችልም" የሚል ምክንያት በመስጠት አታሎታል።
ዲምብልቢም ብዙ ደንቀራዎችን አልፎ ከኢትዮጵያ ከወጣ በኋላም የኢትዮጵያ መንግሥት **አቶ ተፈሪ ወሰን** የተባሉ የማስታወቂያ ሚኒስቴር ባልደረባ የነበሩትን ለንደን ድረስ ተከታትለው እንዲሄዱ ተደርጎ ፊልሙ እንዳይታይ ተሞክሮ ነበር። ያም ሆነ ይህ ፊልሙ ሐሙስ ጥቅምት 8ቀን 1966ዓም ለመጀመሪያ ጊዜ 12ሚሊዮን የእንግሊዝ ሕዝብ እያዩ በእንባ ሲራጭና ወዲያውኑ ንብረታቸውን እየሸጡ እርዳታ ለማድረስ ቀድመው ሲሯሯጡ፣በዚያው ዕለት የኢትዮጵያ ቴሌቪዥን ደግሞ በመጋረጃ በተጋረደው አፅምና ዕልቂት ፊት ዘፈኑና ደስታውን ለመላው የኢትዮጵያ ሕዝብ ያሥተላልፍ ነበር።

የሕዝቡ ማለቅ ሥሜት አይሰጠንም ካልተባለ በስተቀር፣**ይህ የ60ዎቹ ተማሪዎች ትግል ያመጣው ውጤት ነው**።ይህንና ይህንን መሰል ሁኔታዎች ያላገናዘበ ዕውር ትችት የትም አያደርስም።ትናንትና ከትናንት ወዲያ የተወለደውም ሆነ በ60ዎቹ ተወልዶ ጥቅሙ የተነካ፣ በዳይና ገራፊ የነበረ፣የግሉን ሆድ ብቻ እንጅ የሌላው ሥቃይ የማይሰማው እየተነሳ የጭቃ ጅራፉን እንዲያጮህ አንፈቅድም። በአጠቃላይ የ60ዎቹ፣የ60ዎቹ እያለ የሚያላዝነው ይህ የትግሉ አቅጣጫ የጠፋበት ቡድን ሳይዘገይና ሳይመሽ ወደህሊናው ተመልሶ ንቃቱን አዳብሮ ዓላማው ምን እንደሆን መርምሮ ተረድቶ ዓላማው ላይ ያነጣጥር እላለሁ።

ሚዛኑን ያልጠበቀ አካሄድ ብዙ ሲለፈፍ እንሰማለን። አገርን የሚያሥተዳድረው የአፄ ኃይለስላሴ መንግሥት ለርሀቡና በአጠቃላይ ለሠቆቃው ምን አደረገ?ኃላፊነቱን መሸከም የሚገባው መንግሥት ነኝ ብሎ በሥልጣን ላይ የተቀመጠው አይደለም እንዴ? ዛሬ በአገራችን ላይ ለሚደረገው ወንጀል ተጠያቂው መንግሥት ነኝ የሚለው የትግሬ ዘረኛ ቡድን እንጅ ተማሪውና ሕዝቡ እንዳልሆነ ሁሉ በዚያም ጊዜ አገሩን ያሥተዳድር የነበረው መንግሥት እንደሆነ መዘንጋት የለበትም። አንድም ቦታ ላይ እንኳን የአፄ ኃይለሥላሴን መንግሥት ለደረሰው ችግር ተጠያቂ ሳያደርጉ የ60ዎቹ እያሉ ማናፋት ሚዛን አይደፋም።

ምንም እንኳን ብዙዎቻችን በ66ቱ የካቲትም ይሁን ከእሱ በፊት በአነሥተኛው የወጣት ዕድሜ ክልል ውስጥ ብንሆንም ማለት ብሥለቱ አይኑረን እንጅ በፊት ለፊታችን ይደረጉ የነበሩ ሠቆቃዎችን ማዬትና መገንዘብ አላዳገተንም።ለዚህም ነው ረሀቡን፣ችግሩን ወዘተ ማዬት ያልተሳነን።

እርግጥ ነው በተማሪው ንቅናቄ ከአማራው ጋር አብረውን የነበሩት የትግሬና የኦሮሞ ዘረኞች በእኛ ላይ ክህደት ፈፅመው አገራችንን እና ዘራችንን አጥፍተዋል፣እያጠፉም ነው። ለዚህም ነው ዛሬ እነዚህ ከሀዲዎች በተለያዩ መድረኮች ብቅ እያሉ ሲቀባጥሩ የነቃው አማራ ጆሮ የማይሰጣቸውና የወጋ ቢረሳ የተወጋ አይረሳ የሚላቸው።
እነኚህ ነፍሰ ገዳዮች **በኦነግ/በኦዴግ፣ በወያኔ/ታንድ/አረና ትግሬዎች፣ በኢሳት/በግንቦት ሰባት/በጎንደር/በጎጃም/በወሎ ህብረቶች፣ በሸንጎ**፣ወዘተ መሽገው ዛሬም እንደትናንቱ ለማንነቱ የሚታገለውን ቆራጥ አማራ ድጋፍ ለማሳጣት "ብአዴን ነው፣ወያኔ ነው፣ወዘተ" እያሉ አሉባልታና ውሸት ሥለሚያሥራጩ፣ለመንቃት ጊዜ የወሰደበትን የዋህ አማራ፣ግራ ሥለሚያጋቡት "በሬ ከአራጁ ይውላል" እንደሚባለው በተዘዋዋሪም ይሁን በቀጥታ የገዛ ወገኑን አማራውን ለገደሉትና ለሚገሉት ወንጀለኞች ገንዘቡንና ድጋፉን ሲሰጥ ይሥተዋላል። ለእነኚህ የአማራ ወገኖቻችን የምንላቸው ቢኖር "እባካችሁ ግራ ቀኙን መርምሩት፣እነማንን እንደምትደግፉ በጥልቀት ተመራመሩ፣ጠይቁ፣እንደዱሮው  ዕምነት ብቻ አይበቃም፣እናንተ በምትለግሱት ገንዘብና ድጋፍ ወገናችሁን አማራውንና አገሩን አጠፉት"።

*ሥለዚህ እነኚህን ዘረኛ የትግሬና የኦሮሞ ከሀዲዎች እንዲሁም ከአማራው ውስጥም በማስረጃ ከሀዲነታቸው የተረጋገጠ አሉ ከተባለ ያለማመንታት ማውገዝ ተገቢ ነው።*

ነገር ግን በጥቂቶች ምክንያት 60ዎቹ ብሎ በወቅቱ የታገለውንና በቅንነት ለለውጥ የተሰዋውን ብዙሀኑን አብሮ ጨፍልቆ ማቅረብ ትልቅ ሥህተት ነው።

የ60ዎቹ እየተባለ በጅምላ ከሚወነጀለው አማራ ውሥጥ በወቅቱ ለለውጥ የታገለው ከ99 ከመቶ(99%) በላይ በአገር ፍቅር ሥሜት  የተቃጠለ፣ረሀብን፣ችነፈርን፣ችግርን፣ሙስናንና የአስተዳደር በደልን የተጋፈጠ፣ለአገሩና ለሕዝቡ መልካም የተመኘና ንቃቱ ያልፈቀደለት ትውልድ ሲሆን "ከኑግ ጋር ያለሽ ሰሊጥ አብረሽ ተወቀጭ" ሆነና ምናልባት አንድ ከመቶ(1%) በማይሞሉ ጥቂቶች ምክንያት ብዙሀኑን ቅን አሳቢ ጨፍልቆ ማቅረብና ዘላለም መደብደብ ትልቅ አሳፋሪ ተግባር ነው።ለዚህም የተቀደሰ ዓላማ የተሰውትን አማራዎች አፈሩ ይቅለላቸው ከማለት ይልቅ የወደቀ ሬሳ ጧት ማታ እያነሱና እየጣሉ መደብደቡ እና ያለፈውንስ ጧት ማታ እያነሱ ማላዘን ዛሬ ከትግሬ ዘረኞች ጋር ለምናደርገው ግብግብ ጠቀሜታው ምኑ ላይ ነው?

እንዲህ ዓይነቱ የተንሸዋረረ አመለካከት ይከፋፍለናል እንጅ አያሥተቃቅፈንም።  ወያኔ በዘር፣ ግንቦት 7 በጎጥ ከፋፍለውናል።እኛ አማሮች ደግሞ በአንድ በኩል የ60ዎቹ በሌላ በኩል ወጣቶቹ እየተባባልን አንዱ ሌላውን በማግለልና በመወነጃጀል በዕድሜ ለመከፋፈል መታገሉ እጅግ አደገኛ ፅንፈኝነት ነው።

ሥለዚህ በመናናቅ ወጣቱ ያለ60ዎቹ፣እነሱም ያለወጣቱ እንዲዝ ከተባባሉ ትግሉ አይሰምርም።ይህንን የሌለ ልዩነት እንዳለ አድርጎ መንቀሳቀስን ከአይምሯችን ፍቀን በመጣል እጅና ጓንት መሆን ካልቻልን ለአብሮነታችን ጠንቅ ነው።ትግላችንን አንዲት ሚሊሜትር እልፍ አያደርገውም።

ይህ በተደጋጋሚ ከተወሰኑት ከ60ዎቹ ጀምሮ እሥከዛሬው ትውልድ ድረስ እንደገደል ማሚቶ እየተቀባበሉ የ60ዎቹ እየተባለ የአፍ ማሟሻ የሆነውና በጅምላ የሚነዛው ዘመቻ አንድ ቦታ ላይ ልጓም ኖሮት መገታት ካልቻለ በተጨባጭ ላለብን የአብሮነት ትግል ጎጅ ነው ። አንድ ወገን ብቻ ሽምጥ ሲጋልብ ዝም የተባለውና ክርክር ያላስነሳው፣ በአሁኑ ተጨባጭ ሁኔታ እንዲህ ዓይነቱን አንስቶ መነጋገር ጊዜውና ወቅቱ ሥላልሆነ፣ከፊት ለፊታችን ለተደቀነብንም ችግር መፍትሄ ሥለማይሆን፣ከትግሬ ዘረኞች ጋር ለሚዋደቀው ወገናችን የሚያመጣው ጥቅም ሥለማይኖርና የጀመርነውን የአማራውን ትግል መሥመር እንዳያሥተን በመሥጋት እንደሆነ ይታወቅ።

አሁን በአገር ቤት በዱር በገደል ከትግሬ ዘረኞች ጋር የሚዋደቀው ወገናችን የአማራው ሕዝብ ማንነቱንና ህልውናውን ተግባራዊ ለማድረግ ነው።ይህ ሕዝብ ከእኛ የሚፈልገው በቅድሚያ ልዩነታችንን ሳይሆን አንድነታችንን፣ጠባችንን ሳይሆን ፍቅራችንን ነው። ሥለዚህ በአንድነትና በፍቅር ከተሳሰብን በገንዘብ፣በሞራል፣በፅሁፍ ወዘተ እንደርሥለታለን ማለት ነው።

ሥለዚህ ይህንን ከወዲሁ ተገንዝበን እኛ አማራዎች ሁላችንም በአንድነት ቆመን ሙሉ በሙሉ ወደአማራው ወገናችን ካተኮርን ከምድረ ገፅ እንዳይጠፉና ማንነቱን እንዲያስከብር ትልቅ አሥተዋፅዖ በማድረግ ግዴታችንን ተወጣን ማለት ነው።ዳግመኛ እንዳንበላ እንወቅበት።

የአማራ ማንነትና ህልውና ተግባራዊ ይሆናል

አሸናፊ በላይ